መልእክት ሦስት

**እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ግብ**
**አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ለመገንባት**
**ጌታን በቀደመው ፍቅር መውደድ፣ ጌታን እንደ የሕይወት ዛፍ መደሰት**
**እና እንደ የኢየሱስ ምስክር ወርቃማውን መቅረዝ መሆን**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ራእ. 2፥1-7፤ ኤፌ. 6፡24፤ 2 ጢሞ. 1፥15፤ 2 ቆሮ. 11፥2-3፤ ዮሐ. 14፡21፣ 23፤ 21፥15-17

I. **በራእይ 2፡7 ያለው የሕይወት ዛፍ፣ የተሰቀለውና ከሞት የተነሣው ክርስቶስ በእግዚአብሔር ለተዋጁት ሕዝቡ ሁሉ ለዘላለም ሙብል እና ድሰታ ይሆን ዘንድ የሕይወት ዛፍ በሚሆንባት መጠናቀቋ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በሆነው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ዛሬ ያለውን የተሰቀለውን (እንደ ቁራጭ እንጨት በዛፉ የተመለከተው—1 ጴጥ. 2፡24) እና ከሞት የተነሣውን (በእግዚአብሔር ሕይወት የተመለከተውን—ዮሐ. 11፥25) ክርስቶስ ያመለክታል።**

II. **በኤፌሶን ያለችውን ቤተ ክርስቲያን ጨምሮ በእስያ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ከሚያጨው የሐዋርያው ጳውሎስ አገልግሎት ዘወር ብለው ነበር (2 ጢሞ. 1፥15፤ 2 ቆሮ. 11፥2-3)፤ ስለዚህም፣ ከሃያ ስድስት ዓመታት በኋላ አካባቢ ሐዋርያው ዮሐንስ በኤፌሶን ላለችው ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ፣ የቀደመውን ፍቅራቸውን ትተው እና እንደ የሕይወት ዛፍ የክርስቶስን ድሰታ አጥተው ነበር (ራእ. 2፡4-5፣ 7)፦**

ሀ. እውነተኛው የአዲስ ኪዳን አገልግሎት ለሕይወት አቅርቦታችን ክርስቶስን እንደ ሕይወት ዛፍ በቀላሉ በመመገብ እና በመደሰት እያጠነከረን፣ ሁልጊዜም ጌታ ኢየሱስን በቀደመው ፍቅራችን እንድንወደው ያነሳሳናል—2 ቆሮ. 11፥2-3፤ 3፡3-6።

ለ. ጌታን በመጀመሪያው ፍቅር መውደድ፣ በፍቅሩ ግድ በመሰኘት በሕይወታችን እርሱን እንደ ሁሉ ነገራችን እውቅና በመስጠት እና በመውሰድ ለእርሱ ቀዳሚውን ስፍራ፣ የመጀመሪያውን ስፍራ መስጠት ነው—ራእ. 2፡4-5፤ ቆላ. 1፥18፤ 2 ቆሮ. 5፥14-15፤ ማር. 12፡30፤ መዝ. 73፡25-26።

ሐ. ጳውሎስ ለኤፌሶን ሰዎች በጻፈው መልእክት የመደምደሚያ ቃሉ "ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመጥፋት ከሚወዱ ሁሉ ጋር ጸጋ ይሁን" (6፡24) የሚል የጸጋ በረከት ነው፤ በኤፌሶን መጽሐፍ ውስጥ በበለጠገ ስሜት የተሞላው *በፍቅር* የሚለው ቃል በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ውሏል (1፡4፤ 3፡17፤ 4፡2፣ 15-16፤ 5፡2)።

መ. የኤፌሶን መጽሐፍ ግብ እግዚአብሔርን እንደ ፍቅር እንድንደሰተው እና በመለኮታዊው ፍቅር ጣፋጭነት መገኘቱን እንድንደሰት፣ በዚህም ክርስቶስ እንዳደረገው ሌሎችን እንድንወድ የእግዚአብሔር ውስጣዊ ንጥረ-ነገር ወደ ሆነው ፍቅር ውስጥ እኛን ማመምጣት ነው—1፥15፤ 2፡4፤ 3፡19፤ 5፡2፣ 25፤ 6፡23፤ ተዛ. 1 ዮሐ. 4፥16-19።

ሠ. በኤፌሶን ያለችው ቤተ ክርስቲያን ጌታን በመውደድ ጉዳይ ወድቃለች፤ እንዲህ ያለው ውድቀት በዘመናት ሁሉ ለቤተ ክርስቲያን ውድቀት ዋና ምክንያት ነበር—ማቴ. 24፡12፤ ማር. 12፡30-31፤ ተዛ. ዳን. 7፡25።

ረ. በራእይ 2፥1-7 ውስጥ በኤፌሶን ላለች ቤተ ክርስቲያን የጌታ መልእክት አራት ዋና ነጥቦች አሉት፤ እነዚህ አራት ዋና ነጥቦች በእንግሊዘኛው ፊደል በእንግሊዝኛው ፊደል "ኤል" የሚጀምሩ አራት ቃላት ናቸው—*ፍቅር (love)፣ ሕይወት (life)፣ ብርሃን (light) እና መቅረዝ (lampstand)* ናቸው፦

1. የመጀመሪያውን ፍቅር ለመመለስ በሁሉ መንገድ እና በነገር ሁሉ ለጌታ ኢየሱስ ቀዳሚውን ስፍራ መስጠት አለብን፤ ያኔ እርሱን እንደ ሕይወት ዛፍ እንደሰተዋለን፣ ይህም ሕይወት የሕይወት ብርሃን ይሆንልናል—ዮሐ. 8፥12፤ ኤፌ. 5፡8-9፤ 13።

2. ያን ጊዜ እንደ ኢየሱስ ምስክር፣ እንደ ወርቃማው መቅረዝ የምናበራ እንሆናለን፤ ይህ ካልሆነ ግን መቅረዙ ከእኛ ይወሰዳል—ራእ. 1፥9-12፣ 20፦

   ሀ. ወርቃማው መቅረዝ ሦስታንዱን አምላክ ያመለክታል—አብ እንደ ንጥረ-ነገር በወልድ አካል ለብሷል፣ ወልድ እንደ አካል መልበስ በመንፈስ በኩል ተገልጦአል፣ መንፈስ በሙላት እውን የሚሆነው እና የሚገለጠው እንደ አብያተ ክርስቲያናት ነው፣ አብያተ ክርስቲያናትም የኢየሱስ ምስክር ናቸው—ዘጸ. 25፡31-40፤ ዘካ. 4፡2-10፤ ራእ. 1፥10-12።

   ለ. በመለኮታዊው እሳቤ ወርቃማው መቅረዝ ጉብጉቦች እና የለውዝ አበቦች ያሉት ሕያው እና የሚያድግ ዛፍ ነው፤ ስለዚህም በየእለት ምልልሳችን ውስጥ እግዚአብሔር እንደ እውነታ ይገለጥ ዘንድ በባሕሪው መልካም፣ በአካሄዱ ጻድቅ እና በመገለጡ እውነተኛ እንደሆነው የብርሃኑ ፍሬ (የመንፈስ ፍሬ) በእኛ ውስጥ፣ ከእኛ ጋር፣ በእኛ አማካኝነት እና ከእኛ ውስጥ እንደሚያድግ፣ ቅርንጫፍ እንደሚያወጣ፣ እንደሚያቆጠቁጥ እና

እንደሚያብብ ሕያው ወርቃማ የትንሣኤ ዛፍ መቅረዙ በክርስቶስ አካል የለበሰውን ሦስታንዱን አምላክ ያሳያል—ዘጸ. 25፥31፣ 35፤ ኤፌ. 5፥8-9፤ ገላ. 5፥22-23፤ ዮሐ. 12፥36።

ሰ. የሕይወትን ዛፍ መብላት፣ ማለትም ክርስቶስን እንደ የሕይወት አቅርቦት መደሰት በቤተ ክርስቲያን ቀዳሚው ጉዳይ መሆን አለበት፤ ለድሰታችን እንመገበው ዘንድ እና ለእግዚአብሔር መገለጥ በእርሱ እንቀናበር ዘንድ (1፥26፤ ዮሐ. 6፥57፣ 63) ክርስቶስ እንደ ሕይወት ዛፍ "ለመብላት መልካም" ነው (ዘፍ. 2፡9)፡-

1. የቤተ ክርስቲያን ሕይወት ይዘት በክርስቶስ ድሰታ ላይ ይመረኮዛል—ይበልጥ ስንደሰተው፣ ይዘቱ ይበልጥ ይበለጥጋል፤ ነገር ግን ክርሰቶስን መደሰት እርሱን በቀደመው ፍቅር መውደዳችንን ይጠይቃል።
2. ለጌታ ያለንን የቀደመውን ፍቅር ከተውን፣ የክርስቶስን ድሰታ እናጣዋለን፣ የኢየሱስንም ምስክር እንጥላለን፤ ከዚህም የተነሣ መቅረዙ ከእኛ ይወሰዳል—ራእ. 2፥1-7።
3. እነዚህ ሦስት ነገሮች—ጌታን መውደድ፣ ጌታን መደሰት እና የጌታ ምስክር መሆን—አብረው ይሄዳሉ።

**III. የጌታ ምለሳ ጌታን በቀደመው ፍቅር፣ በምርጡ ፍቅር የመውደድ እና እንደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ግብ አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን መገንባት ለሆነው ለሕይወታዊው የክርስቶስ አካል መገንባት ጌታ ኢየሱስን እንደ ሕይወት ዛፍ የመመገብ ምለሳ ነው—ኤፌ. 4፥15-16፤ ራእ. 22፥14፡-**

ሀ. ክርስቶስን እንደ የሕይወት ዛፍ ለመደሰት፣ ሁልጊዜም፣ "ጌታ ኢየሱስ፣ እወድሃለሁ" ብለን ልንነግረው ያስፈልጋል፤ በነገር ሁሉ የመጀመሪያውን ስፍራ እየሰጠነው፣ ለጌታ ኢየሱስ የሚነድ ፍቅር ካለን፣ እርሱ የሆነውን ነገር ሁሉ እንደሰታለን—2፥4-5፣ 7፤ 1 ቆሮ. 2፥9።

ለ. በጌታ ማመን እርሱን እንደ ሕይወት መቀበል ነው፣ ጌታን መውደድ እርሱን እንደ ሕይወት መደሰት፣ የተቀበልነውም ማንነት ራሱን መደሰት ነው፤ እምነት በእግዚአብሔር የተሰጠን ክርስቶስን እንደ ሕይወታችን እንድንቀበለው ነው፤ ፍቅር እንዲህ ያለን ድንቅ እምነት ያመጣል፣ የሦስታንዱን አምላክ ብልጥግናዎች በሙሉ በክርስቶስ እንደ ሕይወት እንድንኖራቸውም ያስችለናል—2 ጴጥ. 1፥1፤ ዕብ. 12፥1-2፤ 2 ቆሮ. 4፥13፤ ገላ. 5፥6፤ ዮሐ. 1፥12-13፤ 21፥15-17፤ ቆላ. 3፥4።

ሐ. በጌታ ኢየሱስ ስናምን የተቀበልነው ያ ሕይወት ማንነት ነው፣ ይህንን ማንነትም የምንተገብርበት እና የምንደሰትበት ብቸኛው መንገድ እርሱን በቀደመው ፍቅር መውደድ ነው፤ ጌታ ኢየሱስ እንደ ሕይወታችን ማንነት ስለሆነ፣ በዚህች አፍታ እና ዕለት ዕለት የአሁን መገኘቱን ለመደሰት ከእርሱ ጋር አዲስ ግንኙነት ያስፈልገናል—ዮሐ. 11፥25፤ 14፥5-6፤ 1 ጢሞ. 1፥14፤ 2 ቆሮ. 5፥14-15፤ ራእ. 2፥4-7፤ ቆላ. 1፥18፤ ሮሜ 6፥4፤ 7፥6።

መ. "ጌታን ለመውደድ ራሳችሁን ስጡ። ከዚህ የሚያይል ሌላ መንገድ የለም፣ ሌላ አንዳች ዋስትና የሚሰጥ፣ እጅግ የበለጠገ እና እጅግ በድሰታ የተሞላ መንገድ የለም። ብቻ እርሱን ውደዱት። ለሌላ ለምንም ነገር ግድ አይበላችሁ"—*Life and Building as Portrayed in the Song of Songs"* ከሚለው መጽሐፍ ከገጽ 23-24 የተወሰደ።

ሠ. እርሱን ስንወደው ራሱን ለእኛ ይገልጥልናል፣ እርሱና አብም ወደ እኛ በመምጣት መኖሪያን ያደርጋሉ (ዮሐ. 14፥21፣ 23)፤ ስለዚህ እንደዚህ ያሉ ጸሎቶችን መጸለይ አለብን፣ "ጌታ ሆይ ፍቅርህን አሳየኝ፣ እንድወድህ እና ለአንተ እንድኖር በፍቅርህ ግድ በለኝ"፤ "ጌታ ሆይ ሁልጊዜም አንተን የምወድህ አድርገኝ"፤ ጌታን ሳናቋርጥ እንዲህ ልንለው ያስፈልጋል፣ "ጌታ ኢየሱስ፣ እወድሃለሁ፤ ጌታ ሆይ በፍቅርህ ጠብቀኝ! በራስህ ማርከኝ! ሁልጊዜም አፍቃሪና የአሁን በሆነው መገኘትህ ውስጥ ጠብቀኝ።"

ረ. ይበልጥ ስንወደው፣ ከእርሱ ጋር ባለን ኅብረት መገኘቱ ይበልጥ ይኖረናል፤ ውስጠ-መሠረታዊ በሆነ መንገድ በጌታ ምለሳ ውስጥ መሆናችን ጌታ ኢየሱስን መውደዳችን ነው፤ እርሱን የማንወደው ከሆነ ከምለሳው ጋር እድል ፈንታ አይኖረንም—መኃ. 1፥1-4፤ 1 ቆሮ. 2፥9፤ 16፥22።

ሰ. በዚህ መሠረት እንዲህ ብለን መዘመር እና መጸለይ አለብን፣ "ጌታዬን እወደዋለሁ፣ ሆኖም በራሴ ፍቅር አይደለም፣/ የምሰጠው የለኝምና፤/ ጌታ እወድሃለሁ፣ ያለኝ ፍቅር ሁሉ ግን ያንተ ነው፣/ በፍቅርህ ነውና የምኖረው" (ከእንግሊዝኛ የመዝሙር መጽሐፍ ቁጥር 546፣ 1ኛ ቁጥር)፤ "እያንዳንዱ የሰው ልብ የሚወደው ነገር/ ኢየሱስ ካልሆነ ማን ሊያርፍ ይችላል፤/ ጌታ ልቤ ላንተ ተሰጥቷል፤/ ውሰደው፣ አንተን አብልጦ ያፈቅርሃልና" (ከእንግሊዝኛ የመዝሙር መጽሐፍ፣ ቁጥር 547፣ 1ኛ ቁጥር)።

© 2022 Living Stream Ministry